# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የፌዴራል እና የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች
## የጤና አገልግሎት ክፍያ አተገባበር
## መመሪያ ቁጥር 920/2014

## Federal and University Hospitals
## User fee Implementation
## Directive No. 920/2022


**የገንዘብ ሚኒስቴር**
MINISTRY Of FINANCE

**ሐምሌ 2014 ዓ.ም**
July 2022

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የፌዴራል እና የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት ክፍያ አተገባበር መመሪያ ቁጥር 920/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **አውጭው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1/ **"የፌዴራል ሆስፒታል"** ማለት ተጠሪነቱ ለጤና ሚኒስቴር የሆነ ሆስፒታል ነው፤

2/ **"ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል"** ማለት በትምህርት ሚኒስቴር ስር የሚገኙ የህክምና አገልግሎት፣ የመማር ማስተማር፤ ጥናት እና ምርምር በቅንጅት የሚሰጥበት ሆስፒታል ነዉ

3/ **"የተመላላሽ ህክምና ክፍል የክፍያ ስርዓት"** ማለት በተመላላሽ ክፍል ዉስጥ ለሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ስርዓት ማለት ነዉ፤

4/ **"የተኝቶ ህክምና ክፍል የክፍያ ሥርዓት"** ማለት በተኝቶ ህክምና ክፍል ውስጥ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ስርዓት ማለት ነዉ፤

5/ **"የፕሮሲጀር አገልግሎት የክፍያ ስርዓት"** ማለት ለማንኛውም ለሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች ለሚደረገዉ የፕሮሲጀር አገልግሎት የሚከፈል

## Chapter One
## General Provisions

1. **Short Title**

This directive may be cited as the "Federal and University Hospitals user fee implementation Directive No. 920/2022."

2. **Issuing Authority**

The Ministry of Finance has issued this directive pursuant to the power vested in it under Article 75 of Financial Administration Proclamation No. 648/2001 (as amended).

3. **Definition**

In this directive, unless the context otherwise requires:

1/ **Federal Hospitals"** Means a hospital accountable to the Ministry of Health.

2/ **"University Hospitals"** Means a teaching hospital under the Ministry of Education that provides health services with the integration of research and other teaching and learning activities.

3/ **Outpatient Department Payment Mechanism"** means a payment system for the health service provided at outpatient department

4/ **"Inpatient Department Payment Mechanism"** means a payment system for the health service provided at inpatient department

5/ **Procedure Service Payment Mechanism"** means a payment system for the any procedure services provided at the hospital.

ክፍያ ማለት ነዉ፤

6/ **"አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች እና መድኃኒት" ማለት ለማንኛዉም የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች እና ለፕሮሲጀር የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች ማለት ነዉ፤**

7/ **"ያለክፍያ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች"** ማለት የህብረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ልምድ ከማሳደግና በጤና አጠባበቅ ረገድ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ማለት ነዉ፤

8/ **"የሪኮንስትክቲቭና ፕላስቲክ ሰርጀሪ እና የኦርቶፔዲክ ክፍል የክፍያ ሥርዓት"** ማለት በሪኮንስትክቲቭና ፕላስቲክ ሰርጀሪ እንዲሁም በኦርቶፔዲክ ክፍል ውስጥ ለሚሰሩ የህክምና አገልግሎቶች የሚከፈል የክፍያ ሥርዓት ማለት ነዉ፤

9/ **"ደንብ"** ማለት በፌደራል እና በዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ለሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 477/2013 ነው፤

10/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ በፌዴራል እና በዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ለሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣውን ደንብ ቁጥር 477/2013 ማስፈጸም ነው፡፡

6/ **"Consumable Supplies and Drugs Payment Mechanism"** means any medical supplies and drugs needed for the procedure.

7/ **Exempted Health Services"** means health services provided free of charge to all people irrespective of level of income by reason of them being public health nature that widely affect the general public and improving the health seeking behavior of the society.

8/ **Reconstructive and Plastic Surgery and Orthopedic Department Payment Mechanism"** means a payment system for the health service provided at reconstructive and plastic surgery and orthopedic department.

9/ **Regulation"** means the regulation No. 477/2021 to determine the payment for medical services provided at federal and university hospitals.

10/ Any expression in the masculine gender in this Directive includes the feminine.

4. <u>**Objective of the Directive**</u>

The main objective of this directive is to create clarification in the implementation of payment for medical services provided at federal and university hospitals.

5. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በማንኛውም የፌደራል እና የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## <u>የአገልግሎት ክፍያ ሥርዓት</u>

6. **<u>የአጠቃላይ የሕክምና አገልግሎት ክፍያ</u>**

የአገልግሎት ክፍያዉ በደንቡ ውስጥ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍያ ሥርዓቱ የሚከተሉትን ታሳቢ ተደርጎ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

7. **<u>የተመላላሽ ህክምና ክፍል ለሚሰጡ አገልግሎቶች የክፍያ ሥርዓት</u>**

1/ በምርመራ ክፍል ዉስጥ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የተካተቱት ለሁሉም አይነት ምርመራ የሚያስፈልጉ የህትመት ወረቀት (Examination paper)፣ የቀጠሮ ካርድ፣ የማፈላለጊያ ካርድ (Tracer card)፣ የካርድ ማቀፊያ (Card folder)፣ የትሪያጅ አገልግሎት፣ የባለሙያ የምርመራና የምክር አገልግሎት፣አገልግሎቱ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የህክምና መሳሪያዎች እና አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች እና ሌሎች ለተመላላሽ ህክምና የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች ታሳቢ ያደረገ ነዉ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርመራ ክፍያዉ (consultation fee) አገልግሎቱን በሚሰጠዉ ባለሙያ ደረጃ የሚለያይ በመሆኑ ህሙማኑ የምርመራ አገልግሎት የሚያገኙበት ክፍል ባለዉ የባለሙያ ደረጃ በደንቡ ላይ በተቀመጠው ክፍያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፣

5. **<u>Scope of Application</u>**

This directive shall be applicable in all Federal and University Hospitals

## Chapter Two
## <u>Payment Mechanism</u>

6. **<u>General Medical Service Payment</u>**

The payment mechanism shall be maintained in accordance with the medical service fee regulation taking in to consideration of the following assumptions.

7. **<u>Outpatient Department Payment Mechanism</u>**

1/ Services included in outpatient department are: - all types of examinations paper (like appointment card, tracer card, card folder), triage service, consultation service, depreciation cost of medical equipment’s, consumables and other required supplies for the outpatient services.

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this Article, consultation fee shall vary according to the level of the health professional providing the service and shall be made in accordance with the fee set out in the regulation by the level of the health professionals in which the patient receives the service.

3/ አገልግሎት ተጠቃሚዉ ለምርመራ በድጋሜ ለአገልግሎት (Revisit consultation) በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በሆስፒታሉ ከመጣ ሌላ የምርመራ ክፍያ መክፈል ሳያስፈልገዉ አገልግሎት ማግኘት ይችላል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛዉም ያለክፍያ ለሚሰጡ አገልግሎት (Exempted health services) ተጠቃሚዎች የምርመራ ክፍያ እንዲከፍሉ አይደረግም፤

## 8. <u>የተኝቶ ህክምና ክፍል ለሚሰጡ አገልግሎቶች የክፍያ ሥርዓት</u>

1/ በተኝቶ የህክምና ክፍል በክፍያ ስርዓት እንዲካተት የተደረጉ አገልግሎቶች የአልጋ አገልግሎት፤ በክፍሉ ዉስጥ የሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች፤የምግብ አገልግሎት፤ የህክምና አገልግሎቱ ሲሰጥ የሚያስፈልጉ የህክምና መሳሪያ እና አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች እና ሌሎች የተኝቶ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ግብዓት ወጪዎችን ያካተተ ነዉ፤

2/ የደንቡ የህክምና አገልግሎት ክፍያ ተመን እንደተጠበቁ ሆኖ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማሟላት እና ሆስፒታሎቹ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ ለማስቻል የአልጋ አገልግሎትን በተመለከተ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ስር የተደነገጉትን ደረጃዎችን መሟላት ያለባቸዉን ግብዓቶች አሟልተዉ ሲገኝ በሁለት ዓይነት ደረጃ የሚከፈል ይሆናል፡-

ሀ) አንደኛ ደረጃ አልጋ ማሟላት ካለበት መስፈርቶች መካከል ለአንድ ታካሚዉ አንድ ክፍል ሆኖ በክፍሉ መሟላት የሚገባቸዉ ንጽህናዉን የጠበቀ የመታጠቢያ ቤት/ መጸዳጃ ቤት (ሳሙና እና ሶፍት ጨምሮ)፤

3/ If the service user comes to the hospital for a revisit consultation within one month, he or she can receive the service without having to pay another examination fee.

4/ Subject to the provisions of sub-article 2 of this Article, exempted health services beneficiaries will not be charged consultation fee.

## 8. <u>Inpatient Department Payment Mechanism</u>

1/ The payment included in the inpatient department are: - bed service, health interventions provided at inpatient department, food service; depreciation cost of medical equipment’s, consumables, and other required supplies for the inpatient services.

2/ Keeping the medical service fee amended at the regulation, in order to meet the needs of the users and to mobilize additional resources for the hospitals, the bed service fee shall be paid at two levels when meeting the requirements set in this sub-article

a) First-class bed requirements are: - one room for each patient with clean bathroom/toilet (including soap and towels), televisions, desks and other basic inputs.

ቴሌቪዥን፣ ጠረንጴዛ እና ሌሎች መሰረታዊ ግብዓቶች ናቸዉ፡፡

ለ) በሁለተኛ አልጋ ደረጃ ደግሞ የጋራ ተኝቶ መታከሚያ ክፍል ሆኖ ንጽህናዉን የጠበቀ የጋራ መታጠቢያ ቤት/ መጸዳጃ ቤት እና ሌሎች በጋራ የሚገለገሉበት መሰረታዊ ግብዓቶች ናቸዉ፤

3/ የአልጋ ክፍያ ተመን ዉስጥ የምግብን አገልግሎትን ይጨምራል፤

4/ ለአገልግሎቶቹ የሚከፈለዉ ክፍያ በእያንዳንዱ በተኝቶ ህክምና ክፍል የሚሰጡ አገልግሎቶች ስር የተዘረዘሩ ክፍያዎችን ታካሚዉ አገልግሎቱን ባገኘበት ቀን ተባዝቶ የሚከፍል ይሆናል፤

5/ በተኝቶ ታካሚ ዉስጥ ለሚሰጠዉ የሁሉም አይነት የነርሲግ አገልግሎት የሚከፈለዉ ክፍያ አገልግሎቱ በተሰጠበት ቀናት ተባዝቶ ይሆናል፤

6/ በተኝቶ ህክምና ክፍል አገልግሎት ተጠቃሚዉ አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት ማስያዥያ ገንዘብ በደንቡ ዉስጥ ያልተካተተ በመሆኑ እንደ ህመሙ አይነት የተኝቶ ህክምና ቆይታ አማካኝ ወጪን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በመጀመሪያ ዙር 40%ቱን ማስያዥያ እንዲሁም በቀጣይ ደግሞ ቀሪዉን 60%ቱን ገንዘብ እንዲያዝ በማድረግ አገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ አማካኝ የማስያዥያ ገንዘብ 100% ማስያዝ የሚችል ተገልጋይ ካለ ገንዘቡን እንዲያሲዝ ተደርጎ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

## 9. <u>የፅኑ ህክምና ክፍል አገልግሎቶች የክፍያ ሥርዓት</u>

በፅኑ ህክምና ክፍል (ICU Department) የሚሰጡ አገልግሎቶች በባህሪያቸዉ የተለየ የህክምና

b) Second class bed requirements are:- shared dormitory with clean shared bathroom and other basic inputs.

3/ The fee for bed services includes food services.

4/ Payment for the inpatient services shall be multiplied by the number days that the patient receives each service with its respective fee.

5/ Payment for all inpatient nursing care shall be multiplied by the number of days provided the service with its respective fee.

6/ In the inpatient ward, before the service is provided, considering the nature of the disease and average cost of inpatient ward, the user shall deposit 40% of the cost of the service at the first round and the remaining 60% in the next round.

7/ Subject to the provisions of sub-article 6 of this Article, if the user can deposit 100% of the average cost of inpatient ward, he or she shall deposit and receive the service

## 9. <u>Intensive Care Unit (ICU) Department Payment Mechanism</u>

The services provided in ICU department are unique in nature, and the payment for bed and

አገልግሎቶች ስለሆኑ በክፍሉ የሚሰጡ የአልጋ እና ሌሎች የሕክምና አገልግሎቶች በተመለከተ ክፍያዉ በደንቡ ዉስጥ በተደነገገዉ የክፍያ ተመን መሠረት እንዲከፍሉ ይደረጋል፤

other medical services shall be in accordance with the regulation

10. <u>የራዲዮሎጂ እና የላብራቶሪ አገልግሎቶች የክፍያ ሥርዓት</u>

የራዲዮሎጂ እና የላብራቶሪ ክፍል ዉስጥ የተዘረዘሩ አገልግሎቶችን ለሚገለገል ማንኛዉም ታካሚ አገልግሎት ባገኘበት ጊዜ ለእያንዳንዱ አገልግሎት በደንቡ የተደነገገዉን የክፍያ ተመን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

**10. <u>Radiology and Laboratory Department Payment Mechanism</u>**

For each of the services listed in the radiology and laboratory department, each patient will be required to pay in accordance with the regulation of each service fee

11. <u>የፕሮሲጀር አገልግሎት የክፍያ ሥርዓት</u>

1/ በየድፓርትመንቱ ለሚሰሩ ለሁሉም ዓይነት ፕሮሲጀሮች (Procedure) የክፍያ ስርዓት በተመለከተ የፕሮሲጀር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች (ግብዓቶች)፤ የህክምና መሳሪያዎች እና ሌሎች የፕሮሲጀር አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በክፍያዉ ዉስጥ የተካተተ ሲሆን ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎቱን ሲያገኙ ከላይ የተጠቀሱትን ግብዓቶች ከዉጭ ከኪስ አዉጥተዉ እንዲገዙ አይደረግም፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፕሮሲጀር ዉጭ የሚታዘዙ መድኃኒቶች (Prescription drugs) በክፍያ ተመኑ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ አገልግሎት ተጠቃሚወቹ እንዲገዙ ይደረጋል፤

**11. <u>Procedure Service Payment Mechanism</u>**

1/ For all types of procedures provided at each department, the depreciation cost of medical equipment, supplies and drugs (used only for procedure) are included in the fee, and the patient will not expect to purchase those inputs out of pocket.

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this article; prescription drugs are not included in the payment and will be covered by the user.

12. **<u>የሪኮንስትክቲቭና ፕላስቲክ ሰርጀሪ እና የኦርቶፔዲክ ክፍል የክፍያ ሥርዓት</u>**

በደንቡ ዉስጥ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1/ በኦርቶፔዲክ ክፍል የተቀመጠዉ የክፍያ ተመን በደንቡ ላይ ለተዘረዘሩት ለቀላል የአንፑቴሽን አገልግሎት ሲሆን በሪኮንስትራክቲቭና ፕላስቲክ ሰርጀሪ ስር የተቀመጠዉ የክፍያ ተመን ደግሞ ከፍተኛ የአንፑቴሽን አገልግሎት ለሚሰጡ አገልግሎቶች ነዉ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ አንፑቴሽን በኦርቶፔዲክ ክፍል የሚሰጥ ከሆነ ወይም ቀላል የአንፑቴሽን አገልግሎት በሪኮንስትራክቲቭና ፕላስቲክ ሰርጀሪ ክፍል የሚሰጥ ከሆነ አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ክፍል ከግምት ዉስጥ ሳይገባ በደንቡ የተቀመጠዉን የክፍያ ተመን ታካሚዉ አገልግሎቱን ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፤

13. **<u>የቃጠሎ ህክምና ክፍል የክፍያ ስርዓት</u>**

በደንቡ ዉስጥ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1/ በቃጠሎ ክፍል (Burn Unit) የተቀመጠዉ የክፍያ ተመን በደንቡ ላይ ለተዘረዘሩት ለከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኝ የቁስል ክብካቤ (Wound care) አገልግሎት ሲሆን በኦርቶፔዲክ (Orthopedics) ክፍል የሚሰጠዉ ደግሞ ለቀላል የቁስል ክብካቤ (Wound care) ማኔጅመንት እና ነርሲንግ አገልግሎት ስለሆነ በተይዩ የተቀመጠዉን ክፍያ ተጠቃሚዉ እንዲከፍል ይደረጋል፤

12. **<u>Reconstructive and Plastic Surgery and Orthopedic Department Payment Mechanism</u>**

Subject to the provisions in the regulation: -

1/ The amputation service provided at orthopedic and reconstructive & plastic surgery department are simple and complex services respectively. Thus, the payment mechanism for reconstructive and plastic surgery shall be for complex amputation services and for orthopedics, the payment shall be for simple amputation services.

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this Article, if the complex amputation service is provided at orthopedic department or if the simple amputation service is provided at reconstructive and plastic surgery department, the patient shall pay the required amount of fee for the service amended in the regulation regardless of the department in which the service is provided

13. **<u>Burn Unit Payment Mechanism</u>**

Subject to the provisions in the regulation:-

1/ The wound care service provided at burn unit and orthopedics department are complex and simple wound care services respectively. Thus, the payment mechanism for burn unit shall be for complex wound care services and for orthopedics, the payment shall be for simple wound care management and nursing care services.

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ደረጃ የቁስል ክብካቤ (Wound care) አገልግሎት በኦርቶፔዲክ (Orthopedics) ክፍል ዉስጥ የሚሰጥ ከሆነ ወይም ለቀላል የቁስል ክብካቤ (Wound care) ማኔጅመንት እና ነርሲንግ አገልግሎት በቃጠሎ ክፍል (Burn Unit) የሚሰጥ ከሆነ አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ክፍል ከግምት ዉስጥ ሳይገባ በደንቡ የተቀመጠዉን የክፍያ ተመን ታካሚዉ የአገልግሎቱን ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፤

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this Article, if the complex wound care service is provided at orthopedic department or if the simple wound care (wound management and nursing care) service is provided at reconstructive and plastic surgery department, the patient shall pay the required amount of fee for the service amended in the regulation regardless of the department in which the service is provided.

## 14. ያለክፍያ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች (Exempted health service)

## 14. Exempted Health Services

1/ በደንቡ ዉስጥ የተካተቱት ያለክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት (Malnutrition) አገልግሎት በተመላላሽም ይሁን በተኝቶ ህክምና አገልግሎት ለሚያገኙ ህጻናት የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቁም፤

1/ In addition to the list of exempted health service in the regulation, malnutrition shall be provided free of charge in outpatient and inpatient department.

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የስጋ ደዌ በሽታ (Leprosy) እና የመጀመሪያ ደረጃ ጾታዊ ጥቃት የጤና አገልግሎቶች (GBV) ያለክፍያ ከሚሰጡ አገልግሎቶች ዉስጥ ተካቶ በነጻ አገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል፤

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this Article, leprosy case shall also be provided free of charge.

3/ በደንቡ ዉስጥ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ያለክፍያ የሚሰጡ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች በሌላ ክፍያ የሚጠየቅበት ተደራቢ ህመም ቢያዙ ለአገልግሎቱ የወጣዉን ወጪ እንዲከፍሉ ይደረጋል፤

3/ In accordance with the provisions of this regulation, if the patient come to the health facility for co-morbidity service, users shall be required to pay the fee of the respective service amended at the regulation.

4/ በዘመቻ እና ወጪዉ በሌላ አካል ለሚሸፈኑ የጤና አገልግሎቶች ያለክፍያ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፤

4/ Service costs covered by the campaign and other party; the service shall be provided without any charge.

## 15. አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች እና መድኃኒት

1/ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶች እና ለፕሮሲጀር የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች በሁሉም አገልግሎቶች ክፍያ ተመን ዉስጥ የተካተቱ ስለሆነ ለአገልግሎት የሚያስፈልጉ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶችን እና ለፕሮሲጀር የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች ተጠቃሚዉ እንዲገዛ (እንዲከፍል) አይደረግም፤ስለሆነም ለአገልግሎት የሚያስፈልጉ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶችን አቅርቦት በሆስፒታሉ ማሟላት ይገባል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሆስፒታሉ ለአገልግሎት የሚዉሉ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶችን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሟላት ባይቻል የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎቹ ከዉጭ ገዝተዉ የሚያቀርቡትን አላቂ የህክምና ቁሳቁስ ወጪን ሆስፒታሉ በሚሸጥበት ዋጋ መጠን ተሰልቶ ለአገልግሎቱ በደንቡ ከተተመነዉ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ህሙማኑ ቀሪዉን እንዲከፍል ይደረጋል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ ከፕሮሲጀር ዉጭ የሚታዘዙ መደሃኒቶች (Prescription drugs) በክፍያ ተመኑ ዉስጥ የተካተቱ ስላልሆነ አገልግሎት ተጠቃሚዉ እንዲገዛ ይደረጋል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገጉት እንደተጠበቀዉ በጥርስ ክፍል ደግሞ Oral and maxillofacial surgery ለመሥራት የሚያስፈልጉ ዉድ የሆኑ የህክምና ቁሳቁሶች በክፍያ ተመኑ ያልተካተቱ ስለሆነ የአገልግሎት ተጠቃሚ አገልግሎቱን በሚያገኝበት ወቅት ከአላቂ ቁሳቁሶች በስተቀር ዉድ የሆኑ የህክምና ቁሳቁሶችን እንዲገዛ ይደረጋል፤

## 15. Drugs and Supplies (Consumables

1/ Since the cost of supplies (consumable) and drugs (used only for procedure) are included at each procedure fee, the user shall not be required to purchase the necessary supplies and drugs out of pocket, while getting the procedure service at all department's.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article, if the hospital is unable to avail the supply and consumables (stock out), the cost of the consumable purchased out of pocket by the service users shall be calculated at the cost of the hospital and the service user shall to pay the differences.

3/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this Article, prescription drugs shall be purchased by the user.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-articles 1 and 2 of this Article, at dentistry department, except consumable (supplies), the user is expected to purchase the required expensive medical equipment's out of pocket while getting oral and maxillofacial surgery.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**16.መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ**

አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት የገንዘብ ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**17.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**18.መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም.*

**አህመድ ሺዴ**

**የኢፌዲሪ ገንዘብ ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**

## Chapter Three

## Miscellaneous Provisions

**16. Amendment of the Directive**

When necessary, the Ministry of Finance will amend the directive.

**17. Non-applicability**

Any directive or practice that is inconsistent with this directive shall have no effect.

**18. Effective date**

This directive shall enter in to force from July 19, 2022

***Addis Ababa July 19, 2022.***

**Ahmed Shide**

**Minister of Finance**
**Minister**